

<u>አሸባሪውን ፈትቶ ሰለማዊውን የሚያሳድድ መንግሥታችንን</u> <u>በአንድ ድምጽ “ተው” እንበለው!!</u>

በስልጤ ዞን በአክራሪ የዉሀቢያ ጂሀዲስቶች እየተካሄደ ያለውን የቤተ-ክርስቲያን መቃጠልና የክርስቲያኖችን ሞትና መገፋት ለማስቆም ዳተኛ የሆነው መንግሥት፣ ድረሱልን የሚሉትን ተጠቂዎች ለአጥቂዎች አሳልፎ በመስጠት አቢያተ-ክርስቲያናትን ሲያስቃጥል የሰነበተው በተቃራኒው ግን በጎንደር ከተማ ባለፉት ዘመናት ለሰላምና ለመረጋጋት ሲደክሙ የነበሩትን ክርስቲያን ወጣቶች በሕግ ማስከበር ስም በማሳደድ ላይ ይገኛል።

የሞዐ ተዋሕዶ ግብረ ኃይሉ በየካቲት 2 ቀን 2014 ዓ.ም ለሚመለከተው መንግስታዊ አካል ያቀረባቸው 7ቱ የኦርቶዶክሳዊያን ጥያቄዎች (https://moaorthodox.com/home/) ላይ እንደተመለከተው ይህ መንግሥት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትናን በሁሉም መንገዶች የማጥቃትና የማስጠቃቱን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ከቀደሙት የደርግና ኢሕአዴግ መንግሥታት በውርስ ተረክቦ እያባባሰ መሆኑን ባለፉት አራት ዓመታት በተጨባጭ አስመስክሯል። ይህ ከመንግሥት መንግሥት እየተሸጋገረና ከአክራሪ ብሔርተኞችና ዉሐቢያና ሌሎች ጽንፈኞች ጋር ተጣምሮ የተባባሰው ጥቃት በአስቸኳይ መዋቅራዊና ሥርዓታዊ መፍትሔ እንዲያገኝ በአደባባይ ጥሪ ቀርቦለታል። ይሁን እንጂ መንግሥት ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያኖች ባለው የተሳሳተ አመለካከትና የርዕዮት ስህተት ችግሩን ከመቀልበስ ይልቅ አባብሶና በስፋት እንደቀጠለበት በያዝነው ወርሃ ሚያዚያ ሶስተኛ ሳምንት በጎንደር የተከሰተን የአክራሪዎች ዉሀቢያ ኢስላሞችን ረብሻ አስቀድሞ ሲታቀድ፣ ትጥቅ ወደ ከተማ ውስጥ ሲከማች እና ገዳዮች ሲደራጁ አስቀድሞ ለመከላከል አልፈቀደም። በዚህ ምክኒያት በጎንደር ከተማ ውስጥ የተከሰተውን ግጭት ወደ ደቡብ ክልል ስልጤ ዞን ተሸጋግሮ አስቀድሞ በተዘረጋው የየአክራሪዎች ሰንሰለታዊ የመናበብ መዋቅራዊ አደረጃጀት ተከትሎ በእኛ በክርስቲያን ወገኖች ላይ የየሚካሄደውን ጥቃት የያዘበት እና የመራበት መንገድ የመንግሥትን መዋቅራዊ አተያይ እና አቋም የበለጠ ያጋለጠ እኩይ ተግባር መሆኑን አረጋግጠናል።

አክራሪ የዉሀቢያ ኢስላም ቡድን ተደራጅቶና ተቀናጅቶ ሰላማዊውን ክርስቲያን በጎንደር ሲያሸብር፤ ቀጥሎም በደቡብ ክልል በስልጤ ዞን ወራቤ ከተማ በማኅበራዊ ሚዲያ እያወጀና እያሳወጀ አቢያተ- ክርስቲያናትን ሲያወድምና ክርስቲያኖችንን ሲያሳድድ፤ሲያስገድል እና የአካል ጉዳት ሰለባ እንዲሆኑ ሲያስደርግ በመንግሥት የደኅንነት መረቡ በኩል ሙሉ መረጃ እንዳለው ማግኘት እየተቻለ ሳይቆጣጠርና ሕጋዊ እርምጃ ሳይወስድ ቀርቷል። ተጠቂዎቹ ክርስቲያኖችም በማኅበራዊ ሚዲያ ድረሱልን ብለው ቢጮኹ እንኳ የፀጥታ ኃይል ሳያሰማራ ቀርቷል። በስልጤ ዞን <u>“ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጠላታችን ነች”</u> በሚል መጽሐፍ እስከማሳተም የደረሰ እና በፅንፈኛነቱ የሚታወቅ ግለሰብን የፀጥታ መዋቅር ኃላፊ አድርጎ በመሾም ጥቃቱን ቀድሞ አመቻችቷል ለዚህም መንግስት ሙሉ ኃላፊነቱን ይወስዳል።

በተቃራኒው ሃይማኖት፤ ጎሣና እምነት ሳይለዩ ከመንግሥት ጋር በመተባበር በአስቸጋሪ ጊዜያት ሁሉ የሕዝቡን ደኅንነት ለመጠበቅ ክርስቲያን ወጣቶችን በማሰባሰብ የሚደክሙ፣ ወንጌል በማስተማር የሚታወቁ፣ ወጣቱ ለመንግሥት በክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር እየታዘዘ እንዲኖር አርአያ በመሆናቸው የጎንደር ሕዝብ የሚያውቃቸውን የጎንደር ወጣቶች **የዞኑ እና የፌደራል መንግሥቱ በሕግ ማስከበር ሽፋን በማሳደድ ላይ ይገኛሉ**። አበው ሲተርቱ አህያውን ፈርቶ ዳውላውን እንዲሉ ዓለም አቀፍ ድጋፍ የሚቸረውን፣ የቱርክ እና የግብፅ መንግሥት እንዲሁም ዓለምዓቀፍ የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ማሽን በሆኑ እንደ የአልጀዚራ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ጭምር የሚዘውሯቸውና የሚንጫጩለትን የአሻባሪ መረብ እንደመቆጣጥር፣ ከአዲስ አበባ እስከ ስልጤ ዞን፣ ጂማና ጎንደር የተዘረጋውን መረብ የሚመሩ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ከማዋል፤ መትረየስና ከባድ መሣሪያ ታጥቆ ከተማ ውስጥ በመከላከያ ላይ የሚተኩሰውን ቡድንና የሃገር ስጋት የሆነውን ከሃዲ፤ በእምነት ካባ ተጀቡኖ የሚያሸብረውን የሽብር ቡድን ከምንጩ ተከታትሎ እርምጃ ከመውሰድና ለፍርድ ከማቅረብ ዳተኝነቱን ያሳዬው መንግስት በተቃራኒው ግን ሰላማዊውን ክርስቲያን ወጣት በማሳደድ ላይ ተጠምዷል።

ይህ ዓይን ያወጣ ፍርደ-ገምድልነትና ለወደፊቱ ኦርቶዶክሳዊያንን ለበለጠ ጥቃት ለማመቻቸት በሚመስል አካሄድ ክርስቲያኖች በምንም መንገድ የመሰባሰብና የመደራጀት ሙከራ እንዳያደርጉ ሰላማዊ ክርስቲያን ወጣቶችን ማሳደዱ ከፍተኛ ሥጋትን በክርስቲያኖች ላይ መፍጠር ብቻ ሳይሆን በተግባር እየታየ ስለሆነ ***<u>ክርስቲያኖች ሁሉና የመንጋው መሪዎች ጳጳሳት እንዲቃወሙት</u>*** ***<u>የሞዐ ተዋህዶ ግብረ-ኃይል ጥሪውን ያቀርባል።</u>***

በዚህ አጋጣሚ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች፣ የአገልግሎት ማኅበራት፣ የሰንበቴና የፅዋ ማኅበራት፣ ሰባኪያነ ወንጌል፣ የአብነት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና መምህራን፣ ለፍትሕና ለእውነት ዋጋ የምትሰጡ የሌላ እምነት ተከታዮች ይህንን መንግስታዊ አድልዎና ለዉሐቢያ አክራሪ ኢስላም ጥቃት ሽፋን የሚሰጥ አካሄድ በአንድነት በማውገዝ አገራችን አሁን ላይ እየተንደረደረች ካለችበት ጥፋት ለመታደግ ለሚጥሩት ሁሉ ተጨማሪ አቅም እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ሞዐ ተዋሕዶ ሚያዚያ 22 ቀን 2014 ዓ.ም ፣አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ